በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሳይንስና ከፍተኛ ትምህርት ሚኒስቴር
ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርስቲ

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of science &hiegher Education
Debre Markos University

# ለ3ኛ ጊዜ የወጣ የጨረታ ማስታወቂያ

*ደ/ማ/ዩ/ብ/ግ/ጨ/01/2016*

የደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በ2016 በጀት አመት ለ1 ዓመት የሚቆይ ለዋናው ግቢ ፣ለጤናና ህክምና ካምፓስ እና ለቡሬ ካምፓስ ለተማሪዎች ምግብ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶችን ማለትም፡-

- ሎት 1- የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ
- ሎት 2 - አትክልት
- ሎት 3 - ፋብሪካ ውጤቶች
- ሎት 4 - እንጀራ ብር
- ሎት 5 - የባልትና ውጤቶች
- ሎት 6 - ስጋ
- ሎት 7 - የማገዶ እንጨት
- ሎት 8 - ዘይት በግልጽ ጫራታ አወዳድሮ መግዛት ይፈልጋል፡፡

ስለሆነም ፡-

1. በዘመኑ እና በዘርፉ የታደሰ የንግድ ስራ ፈቃድ፡ የግብር ከፋይነት የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ እና የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ የሆኑ እና የተመዝጋቢነት ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤
2. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ በተ.ቁ 1 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻ ሠነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው፡፡
3. ተጫራቾች ዋጋ ሞልተው ሲመልሱ ለጨረታ ማስከበሪያ የሚሆን፡-
    - ለሎት 1- የምግብ ሸቀጣ ሸቀጥ ብር 80,000.00/ስማኒያ ሽህ ብር/
    - ለሎት 2 - አትክልት ብር 60,000.00/ስድሳ ሽህ ብር/
    - ለሎት 3 - የፋብሪካ ውጤቶች ብር 100,000/አንድ መቶ ሽህ ብር/
    - ለሎት 4 - እንጀራ ብር 60,000/ስልሳ ሽህ ብር/
    - ለሎት 5 - የባልትና ውጤቶች 100,000/አንድ መቶ ሽህ ብር/
    - ለሎት 6 - ስጋ 100,000/አንድ መቶ ሽህ ብር/
    - ለሎት 7 - የማገዶ እንጨት 50,000/ሃምሳ ሽህ ብር/
    - ለሎት 8 - ዘይት 60,000/ስድሳ ሽህ ብር/ በባንክ በተረጋገጠ ሲፒኦ ወይም በሁኔታ ላይ ያልተመሰረተ የባንክ ዋስትና በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ስም አሰርቶ ማቅረብ የሚችል ፡፡
4. ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች ሁሉ የጨረታ ዶክመንቱን ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ አስተዳደር ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ወይንም አዲስ አበባ 4 ኪሎ ከቅድስት ማሪያም ቤ/ክርስቲያን ወረድ ብሎ ሮሚና ካፌ ላይ 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 7 ከሚገኘው ቢሮአችን ማስታወቂያው በአዲስ ዘመን ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ 21 ተከታታይ ቀናት የማይመለስ ብር 300.00/ ሶስት መቶ ብር/ ለእያንዳንዱ ሎት በመክፈል መግዛት ይችላሉ፡፡
5. የጨረታውን ፋይናሽያል ኦርጅናል እና ኮፒ ዶክመንት በተለያየ ፖስታ በማሸግ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡
6. አሸናፊው ድርጅት አሸናፊነቱ በተገለፀለት ከ7 ተከታታይ የስራ ቀናት በኋላ ከ8ኛ ቀን ጀምሮ በተከታታይ 8 የስራ ቀናት ውስጥ በግንባር ቀርቦ አሸናፊ የሆነበትን ጠቅላላ ዋጋ 10% የውል ማስከበሪያ በማስያዝ ውል መያዝ የሚችል መሆን አለበት፡፡
7. ተወዳዳሪዎች የጨረታ ሰነዱን በአግባቡ በመሙላትና የሁሉንም ሎቶች ለየብቻ በማሸግ ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ድረስ በመቅረብ ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ከተከታታይ 21 ቀናት በኋላ በ22 ኛው ቀን ከጠዋቱ 3፡59 ድረስ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ማስገባት ሲኖርባቸው ጨረታው በዚሁ እለት ከጠዋቱ 4፡00 ሰዓት ላይ ተዘግቶ ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት 4፡30 ላይ በደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ህንፃ ቁጥር 27 ቢሮ ቁጥር 10 ውስጥ ይከፈታል፤ነገር ግን የጨረታ መዝጊያ እና መክፈቻ ቀኑ የበአል ቀን ወይም ቅዳሜ እና እሁድ ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን ይሆናል፡፡ ሆኖም ተጫራቾች በጨረታው ላይ መገኘት ካልቻሉ መስፈርቱን እስካሟሉ ድረስ ጨረታው ላይ ያልተገኙ ተጫራቾች ፖስታ ጨምሮ በእለቱ ይከፈታል፡፡

የበለጠ መረጃ ለማግኘት በስልክ ቁጥር 058 771 66 91 ደውለው መጠየቅ ይችላሉ፡፡
ዩኒቨርሲቲው ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው

ደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ



Debre Markos University Procurement Administration Process No 1